የኢትዮጵያ ሕዝባዊ እምቢታ ተጀምሯል። ሕዝቡ ተነስቷል። እርስዎ የት አሉ?

# እሰከመቼ

መጋቢት ፲፰ - መጋቢት ፳፬ ቀን ፳፻፫ ዓ. ም. ቅፅ ፫ ቁጥር ፬
March 27 - April 2, 2011
Vol. III, No. 4

## የኢሕአዴግ የአሥራ አራት ከተሞች "የሀገር ልማት ስብሰባ"

ልማት ለኢትዮጵያዊያን የተለየ ትርጉም አለው። የሀገራችን መልማት እንዳሹሪት የያንዳንዳችንን አቅል ወደ አንድ ማዕከል ይስበዋል። አንድ የሚያደርገን፣ ከራሳችን በላይ ሀገራችንን የምናነሣበት፣ ለወገናችን ያለንን ፍቅር መግለጫ መስካችን ነው። ለዚህ ነው ያሁኗ እስከመቼ በአሜሪካ የሚደረገውን የኢሕአዴግ የአሥራ አራት ከተሞች "*የሀገር ልማት ስብሰባ*" የምትመረምረው።

በጠቅላላው በዓለም፣ በተለይ ደግሞ በመጡበት በአሜሪካ ያለነውን ኢትጵያዊያን ስለ ሀገራችን ልማት ከማነጋገራቸው በፊት፣ እኛ ለምን ባለንበት ሁኔታ ተገኘን? ባለንበት ቦታ መደላደል አግኝተን በኑሯችን ተሳክቶልን ለልማት የምናውለው ንብረት ማካበት ከቻልን፣ ቁም ነገሩ ያለው ካገኘነው ከንብረታችን ሣይሆን ከሰዎቹ መሆን አለበት። እንዲህ የሚታሰበው በቀና ሲሚለከቱተ ነው።

ኢትዮጵያዊያን በዓለም ዙሪያ፣ የራሳችን የዕለት ኑሮ እያቸነፍን፣ ለዘመዶቻችን የኑሮ መደጎሚያ እንልካለን። አሁን ከዚያ አልፎ ተጨማሪ ላኩና ትርፍ ታገኛላችሁ ተብለናል። የሀገሪቱ ብር አቅም በየጊዜው የሚያደርገው መኮስመንና በሀገሪቱ ያለ ንብረት አስተማማኝነት ማጣት ይህን አጋልጠ ራቁቱን እንደሚያስቀረው ለማወቅ ልዩ ዕውቀት አይጠይቅም። ታዲያ ይህ እንኳንስ ለሁሉን አዋቂዎቹ ለኢሕአዴግ መሪዎቹ ቀርቶ ለኛ ግልፅ የሆነ ሃቅ ከፊታችን ተጋርጠ፣ የመሪ ድሀ የሆነችውን ሀገራችንን ሀብት በከፍተኛ ደረጃ በማውጣት ይህ "*የሀገር ልማት ስብሰባ*" ለምን አስፈለገ?

ንቀትና ጀሮ ዳባ ልበስ ብሎ ራስን ማደናቆር፣ ከሕዝብ ተገንጥለው፣ ሕዝብን ንቀውና፣ ሕዝብን ረግጠው የሚገዙ አረመኔ አምባገነንችኖች መለያ ባህሪያቸው ነው። እናም እንደ ቱንስያው መሪ፣ እንደ ግብፁ መሪ፣ እንደ የመኑ መሪ፣ እና እንደ ሊቢያው መሪ፣ *"ሕዝቡ እኔን ይወደኛል። ሕዝቡ እኔን በከፍተኛ ድምፅ መርጦኛል። በሀገራችሁ ሰላምና መረጋጋት አለ። ገንዘባችሁን አምጡና ብዙ ትርፍ ታገኛላችሁ።"* ሲል መለስ ዜናዊ፣ ተረኛው መሪ፣ ለኛ ስድብ ነው።

ለኢሕአዴግ የአሥራ አራት ከተሞች "*የሀገር ልማት ስብሰባ*" የመጡት፣ ሕዝቡ የሀገሩ ውድቀት መቆም አለበት ብሎ፣ የዘረኛና ከፋፋይ አገዛዝ ይውደም ብሎ፣ የራሴን ተወካይ በነፃ መርጬ የራሴን መንግሥት በአምባገነኖች መቃብር ላይ አቋቁማለሁ ብሎ ለመሠረታዊ ለውጥ ትግል እንዳይነሣ ቅድመ ማጨናገፊያ ለማድረግ ነው። የታሪክን ጎርፍ ሊያቆም የቻለ የለም። ቤን አሊ ሞከረ አልቻለም። ሙባረክ ከጭካኔ ጋር ሞከረ አልቻለም። ጋዳፊ ከአረመኔያዊ ጭፍጨፋ ጋር እየተሟሟተ ነው፣ ነገ ፍፃሜውን ያገኛል። ምን አልባት የአሜሪካን መንግሥት ለማታለል እየሞከረ ይሆናል። አልሰሜን ግባ በለው! ይባላል። ጥቅማቸውን ዓይተው ወዳዘነበው መንሸራተታቸውን ከግብፅ ይመለከቷል።

በውጭ ሀገር ያለን ኢትዮጵያዊያን ገንዘባችን ለዘመዶቻችን መላክ ብቻ ሣይሆን ዘመዶቻችን የሚኖሩበትን ሁኔታ እናውቃለን። ኦሮሞዎች ነን፣ አፋሮች ነን። ሶማሊዎች ነን፣ አማራዎች ነን። ትግሬዎች ነን፣ ወላይታዎች ነን። ሲዳማዎች ነን፣ አኙዋኮች ነን። ከሁሉ በላይ ደግሞ ኢትዮጵያዊያን ነን! በአንድነት።

ኢትዮጵያዊያን ተነሣስተዋል። ያነሣሣቸውና የሚመራቸው ብሶታቸውና ኢትዮጵያዊነታቸው ነው። አሁንም የታሪክን ወዠብ የሚያቆመው የለም። ጊዜው ደርሷልና።

eske.meche@yahoo.com
ሒሊና ነጋሳ፣
የእስከመቼ ምክትል አዘጋጅ።